የሰ/መ/ቁ.125245

መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች- ረታ ቶሎሳ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

አብዩ ካሳሁን

ፀሃይ መንክር

አመልካች - የድሬደዋ ደ/ምህረት ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል - አልቀረቡም

ተጠሪ - 1ኛ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን - ነ/ፈ አባ ገ/ስላሴ ጌትነት ቀረቡ

2ኛ. በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ የቤቶችና ህንፃዎች አስተዳደርና ልማት ድርጅት

ነ/ፈ ወንድሙ መለሰ ቀረቡ

3ኛ. የድሬዳዋ አስተዳደር መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ -

ነ/ፈ ጀማል ኢብራሃም ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር የተጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት፡- በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ትርፍ የከተማ ቤትና ቦታ ሲወረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የተለያዩ ት/ቤቶች እና ቤቶች የተወረሱባት ሲሆን የድሬደዋ ደ/ምህረት ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል ደግሞ በቤተክርስቲያኗ ስር ካሉት አድባራት መካከል በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 03 እና 04 በባለቤትነት ይዞ የሚያስተዳድራቸው ቤቶች የተወሰዱበት አንዱ አጥቢያ ቤ/ያን ነው፤ የደርግ መንግስት ከወደቀ በኋላ ቤተክርስቲያኗ ባደረገችው ጥረት መሰረት መንግስት በሰጠው ውሳኔ ከየካቲት 1/1987 ዓ.ም ጀምሮ ያላግባብ የተወሰዱት ንብረቶች እንዲመለሱ ጥቅል ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን ዝርዝር

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አፈፃፀሙን የሚመራ እና የሚከውን ከጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት፣ ከስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር፣ ከቤተክርስቲያኗ መንበረ ፓትሪያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና ከኪራይ/መንግስት ቤቶች አስተዳደር ኤጀንሲ የተውጣጣ ኮሚቴ ተዋቅሮ ባደረገው ዝርዝር ጥናትና ባቀረበው መረጃ መሰረት በተለያዩ ከተሞች የሚገኙት የቤተክርስቲያኗ ት/ቤቶች እና ህንፃዎች ተመልሰዋል፤ በድሬዳዋ ከተማ የሚገኙ 29 ቤቶችም በቀረበው ጥናት መሰረት ከመጋቢት 01/1995 ዓ.ም ጀምሮ ለቤተክርስቲያኗ ተመልሰዋል፤ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በድሬዳዋ ከተማ ከተረከበቻቸው 29 ቤቶች መካከል ቀደም ሲል ንብረትነታቸው የድሬደዋ ደ/ምህረት ቅዱስ ሚካኤል ካቴድራል የሆኑትንና ከቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ጋር ተያይዘው ያሉ ስድስት ቤቶችን ወዲያውኑ ለካቴድራሉ ስታስረክብ ቀሪዎችን ቤቶች በተመለከተ ደግሞ የደርግ መንግስት ሲያደርግ እንደነበረው በየወሩ ብር 525.50 ለካቴድራሉ እየከፈለች ቆይታለች፤ ከሳሽ በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 04 የሚገኙት የቤት ቁጥራቸው 011፣ 012፣ 013/01/ሀ፣ 013/02/ለ እና 014 የሆኑት ቤቶች የቀድሞው የድሬዳዋ ደብረ ምህረት ቅዱስ ሚካኤል ንብረቶች መሆናቸውን በማመን ቤቶቹ እንዲመለሱ ባደረገው ጥረት የቤተክርስቲያኗ የበላይ አስተዳደሮች ጉዳዩን አምነውበት አምስቱ ቤቶች ለከሳሽ እንዲመለሱ ተደርጎ ካቴድራሉ የልማት ዕቅድ አውጥቶ ተከራዮችን በማስለቀቅ ሥራውን ጀምሮ ነበር፤ የቤቶቹ መመለስ ለ2ኛ ተከሳሽ ተገልጾለት ተከራዮች እንዲለቁ በማድረግ እና አማራጭ ቤት እንዲያገኙ ለድሬዳዋ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት ደብዳቤ የጻፈ ሲሆን 3ኛ ተከሳሽ በአምስቱ ቤቶች ለካቴድራሉ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰጥ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ምላሽ ሳይሰጥ ለረዥም ጊዜ ቆይቷል፤ በተጨማሪም በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 03 የሚገኙ ቀድሞ የካቴድራሉ ንብረቶች የነበሩ የቤት ቁጥራቸው 0127፣ 0128፣ 0129፣ 0131፣ 0132፣ 0133፣ 0134 እና 0135 የሆኑና የቤት ቁጥር የሌለው አንድ ቤት እና በቀበሌ 04 ገንደቆሬ ተብሎ በሚጠራው ቦታ የሚገኙ ቁጥራቸው 003፣ 004፣ 005፣ 006 (በድሮው) የሆኑ ቤቶች ከሀገሪቱ ህጎች እና ከቤተክርስቲያኗ መተዳደሪያ ደንብ/ቃላዋዲ/ ከሚያስቀምጠው ስርዓት ውጭ በማዕከል ደረጃ በቤተክርስቲያኗ እየተዳደሩ እና ገቢያቸው እየተሰበሰበ ይገኛል፤ 3ኛ ተከሳሽም ለከሳሽ የተመለሱትን አምስት ቤቶች ጨምሮ የይዞታና የባለቤትነት ማረጋገጫዎች አዘጋጅቶ የሰጠ ሲሆን ይህን ማድረጉ የሚመራባቸውን ህጎች የሚቃረን ህገወጥ ተግባር ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ስለሆነም 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች በህገወጥ መንገድ ይዘው እያከራዩ የገንዘብ ጥቅም እያገኙባቸው ያሉትንና በ3ኛ ተከሳሽ በህገ ወጥ መንገድ ካርታ ያወጡባቸውን በድሬዳዋ ከተማ ቀበሌ 03 የሚገኙትን 9 ቤቶች እንዲሁም በቀበሌ 04 ገንደቆሬ የሚገኙትን 4 ቤቶች ባለቤት አለመሆናቸው ተረጋግጦ ለካቴድራሉ እንዲመልሱ፤ አላግባብ የተሰጠው የባለቤትነትና የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰረዝ፤ እንዲሁም ትክክለኛ ባለቤት እና ባለይዞታ ለሆነው ከሳሽ ካርታው እንዲሰጥ በፍርድ እንዲወሰን ጥይቀዋል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ለክሱ ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከሳሽ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ስር የሚተዳደር አንዱ የቤተክርስቲያኒቱ አስተዳደራዊ የመዋቅር ክፍል ነው፤ የሚመራውም ሆነ የሚተዳደረው የቤተክርስቲያኒቱ የበላይ ኃላፊና ህግ አውጪ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ ከአሁን ቀደም ባወጣቸው እና ወደፊትም በሚያወጣቸው ህጎችና መመሪያዎች ነው፤ ቤተክርስቲያኗ የራሷን ተቋም የምትመራውም ሆነ የምታስተዳድረው ያለምንም ጣልቃ ገብነት በራሷ ህግና መመሪያ መሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 11(3) እና 27(2) ተደንግጓል፤ በመሆኑም በሃይማኖት ተቋማት ውስጣዊና ተቋማዊ የንብረት አስተዳደር ላይ የመንግስት አንዱ ክፍል የሆነው ፍ/ቤት ጣልቃ ገብቶ አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችል የሥረ ነገር ሥልጣን የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሌሎች የክስ መቃወሚያዎችም ቀርበዋል፡፡

አመልካች ከፍሲል ለተጠቀሰው መቃወሚያ በሰጠው መልስ እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በፍ/ብ/ህ/ቁ 398 እና 399 እና በቃለ አዋዲው አንቀፅ 3(5) መሰረት የህግ ሰውነት ያለው በመሆኑ በራሳችን ክስ ለማቅረብ ጥቅምም ችሎታም አለን፤ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 መሰረት በፍርድ ቤት ሊያልቅ የሚገባው ጉዳይ ወደ ፍርድ ቤት መቅረቡ በአግባቡ ሲሆን ፍርድ ቤቶች የመወሰን ስልጣን የማይኖራቸው ሃይማኖታዊ ጉዳይ ሲሆን ብቻ ነው፤ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ለፍርድ የቀረበው የንብረት ባለቤትነት ክርክር በመሆኑ ፍርድ ቤቱ የመወሰን ስልጣን አለው፤ የንብረት አስተዳደርን በሚመለከት ቤተክርስቲያኗ ህግ ቢኖራት እንኳ ከህገ መንግስቱ አንቀፅ 40 አኳያ ሲታይ ተቃራኒ ከሆነ ሊዳኝ የሚገባው በዝርዝር ህጎች ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የክስ መቃወሚያ ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የስር ፍርድ ቤት ክርክር እና ማስረጃውን መርምሮ በመጨረሻ ባሳለፈው ብይን፡-

*ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም*

- ለክሱ ምክንያት የሆኑት ቤቶች አስቀድመው ንብረትነታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የነበሩና በደርግ መንግስት በአዋጅ ቁጥር 47/67 ተወርሰው የነበሩ፤ የደርግ መንግስት መውደቁን ተከትሎ ቤተክርስቲያኗ የተወረሱባት ንብረቶች እንዲመለሱላት በተደጋጋሚ ባቀረበችው ጥያቄ የሽግግር መንግስቱ የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት የጥያቄውን አግባብነት ተመልክቶ አላግባብ ተወርሰው በኪራይ ቤቶች አስ/ር ድርጅት ስር ይተዳደሩ የነበሩት ንብረቶቿ እንዲመለሱላት ውሳኔ ከተሰጠባቸው ንብረቶች ውስጥ የሚገኙና ለቤተክርስቲያኗ የተመለሱ መሆናቸው ላይ በግራ ቀኙ መካከል ክርክር እንደሌለ፤
- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ግንቦት 11/1998 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ተወርሰው የነበሩት ቤቶችና ህንፃዎች በቅደም ተከተል በመመልስ ላይ ቢሆኑም በስርአት ካልተመሩ እና ዘመናዊ አሰራር ባለው መልኩ ካልተያዙ በአሰራሩ ችግር እንደሚፈጠር ታውቆ ተዘጋጅቶ በቀረበው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የቤቶችና ህንፃዎች አስተዳደር ልማት ድርጅት የስራ መመሪያና ደንብ መሰረት እንዲመራ ውሳኔ ያስተላለፈ ስለመሆኑ የቀረበው የሰነድ ማስረጃ እንደሚያስረዳ፤
- በተሻሻለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ህገ ቤተክርስቲያን መሰረት ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተክርስቲያንቱ መንፈሳዊና አስተዳደራዊ ህግ አውጭ እና ወሳኝ አካል መሆኑ፤ በቤተክርስቲያኒቱ የመጨረሻው ከፍተኛ የስልጣን ባለቤት መሆኑ፤ በህገ ቤተክርቲያኑ ባልተካተቱ ሌሎች ጉዳዮችም ላይ የመወሰን ሙሉ ስልጣን ያለው በመሆኑ፤
- ቤተክርስቲያኗ ከቅዱስ ሲኖዶስ እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲን ከላይ ወደታች የሚወርድ መዋቅር ያላት ስለመሆኑ፤ ህገ ቤተክርስቲያኑ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን እምነት ሥርዓት ትውፊት መሰረት አድርገው በየትኛውም የአለም ክፍል በተቋቋሙና በሚቋቋሙ ጋዳማት፣ አድባራት፣ አጥቢያ ቤተክርስቲያናት፤ በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኙ የቤተክርስቲያኗ አገልጋዮች እና ሰራተኞች፣ ምዕመናት እና ምዕመናን እንዲሁም በቤተክርስቲያኗ ሥር ልማትን እና እድገትን ለማፋጠን በተቋቋሙና በሚቋቋሙ መንፈሳዊ ኢኮነሚያዊ ማህበራዊ ተቋማት ላይ ሁሉ ተፈፃሚነት ያለው መሆኑ መመልከቱን፤

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

- ተወርሰው የነበሩ የቤተክርስቲያኗ ንብረቶች በመንግስት ውሳኔ ሲመለሱ የንብረቶቹን አስተዳደር በተመለከተ በቤተክርስቲያኒቱ ማዕከላዊ አሰራር ሥር ሆነው እንዲያዙ ውሳኔ የተሰጠው በቅዱስ ሲኖዶሱ መሆኑን፤
- በህገ ቤተክርስቲያኒቱ መሰረት ቅዱስ ሲኖዶስ በቤተክርስቲያኒቱ የመጨረሻው ከፍተኛው የስልጣን ባለቤት እንደመሆኑ መጠን የንብረቶቹን አስተዳደር በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ እንደሆነና ውሳኔውንም ከቅዱስ ሲኖዶስ በታች ያሉት መዋቅሮች ሊያከብሩት የሚገባ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መገንዘቡን፤
- ቤተክርስቲያኗ በራሷ ንብረት አስተዳደር ላይ የምትወስነውን ውሳኔ ፍርድ ቤቱ በመንፈሳዊም ሆነ በአለማዊ ህግ ተመልክቶ ህጋዊ ነው ወይስ አይደለም ብሎ መወሰን በህገ መንግስቱ አንቀጽ 11 መንግስትና ሀይማኖት የተለያዩ ናቸው፣ መንግስት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም ተብሎ የተቀመጠውን ህገ መንግስታዊ መርህ መፃረር መሆኑን፤
- በአጠቃላይ ጉዳዩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የመጨረሻው ከፍተኛው የስልጣን ባለቤት በሆነው በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑና የተሰጠውን ውሳኔ ፍርድ ቤቱ በአለማዊም ሆነ መንፈሳዊ ህግ መሰረት አይቶ ትክክል ነው አይደለም ብሎ ለመወሰን የሚያስችል የዳኝነት ስልጣን የሌለው በመሆኑ እንዲሁም ከሳሽ በፍ/ቤት ዳኝነት የጠየቀባቸው ጉዳዮች በቤተክርስቲያኗ ህግ ታይተው ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ስለሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለውም በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

በዚህ ብይን ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ብይኑ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው ለዚህ ችሎት የቀረበው ይህን በመቃወም ነው፡፡

በአመልካች የቀረበው የሰበር ማመልከቻ በአጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ በአመልካች የቀረበውን አቤቱታ አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሥር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ብይን ተገቢነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በአብላጫ ድምጽ ተወስኗል፡፡ በዚህ መሰረት ግራ ቀኙ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር በፅሁፍ ተለዋውጠዋል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ቅሬታ ከቀረበበት ብይን፣ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ተገቢነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት አከራካሪውን ጉዳይ ለመወሰን የዳኝነት ስልጣን የለኝም የሚል መደምደሚያ ላይ የደረሰው ጉዳዩ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የመጨረሻው ከፍተኛው የስልጣን ባለቤት በሆነው በቅዱስ ሲኖዶስ ግንቦት 11 ቀን 1998 ዓ.ም ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን፤ በዚህ መልኩ የተሰጠውን ውሳኔ ተገቢነት ፍርድ ቤቱ ሊመረምር የማይገባ መሆኑን፤ እንዲሁም አመልካች ዳኝነት የጠየቀባቸው ጉዳዮች በቤተክርስቲያኗ ህግ ታይተው ውሳኔ የሚሰጥባቸው መሆናቸውን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

አመልካች በበኩሉ በሰበር ቅሬታው የሥር ፍርድ ቤት ሲኖዶሱ ግንቦት 11 ቀን 1998 ዓ.ም ወስኗል በማለት ማስረጃውን ወደ መመዘን መግባቱ የሙግት አመራር ሂደቱን ያልተከተለና በሥነሥርዓት ህጉ ከተቀመጠው አካሄድ የወጣ ከመሆኑም በላይ የበኩሉን አስተያየትና ክርክር እንዲያቀርብ እንኳ ሳይደረግ የመጨረሻ ውሳኔ ተሰጥቶበታል ተብሎ የተደረሰበት መደምደሚያ የህግ ስህተት መሆኑን፤ የፍርድ ቤቱ ስልጣን የሚወሰነው በአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 3 ስር በተዘረዘሩት ጉዳዮች እና አካላት ላይ ሲሆን የሚሰሩትም በአዋጁ አንቀፅ 6 እና 7 በተዘረዘሩት ህጎች መሆኑንና የስር ፍርድ ቤት ሥልጣን የለኝም ያለው በማስረጃ መስማት ሂደት መታየት የነበረበትን በ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የቀረበውን ማስረጃ መሰረት በማድረግ ከሥነ ሥርዓት ህጉ ውጪ በመመልከት በመሆኑ፤ እንዲሁም አመልካች ዳኝነት የጠየቀባቸው ጉዳዮች የንብረት ባለቤትነትን እና የመሬት ይዞታን የተመለከቱ በመሆናቸው በዝርዝር ህጎች ታይተው ዳኝነት ሊሰጥባቸው የሚችሉ እንጂ ኃይሚኖታዊ ጉዳይ ስላልሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 11(3) ስር መንግስት በኃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም የሚለው ድንጋጌ የሚመለከተው አይሆንም፣ ጉዳዩም የኃይማኖት ህጎችን ማየትና መመርመር የሚጠይቅ አይደለም ስለሆነም የስር ፍርድ ቤት ብይን የሀገሪቱን ህጎች ያገናዘበ አይደለም በማል ተከራክሯል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 245(1) እና (2) እንደተደነገገው ተከሳሽ ለክሱ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ባቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤቱ መቃወሚያውን ተቀብሎ ሌላው ተከራካሪ ወገን በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበውን ክርክር ከሰማ በኋላ ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ መስሎ የሚገምተው

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ማስረጃ እንዲቀርብለት አድርጎ የቀረበው መቃወሚያ ተገቢና በቂ በሆነ ማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ፍርድ ቤቱ የገመተ እንደሆነ እንደመቃወሚያው ሁኔታ ክሱን ዘግቶ ባለ ጉዳዮችን እንደሚያሰናብት ወይም መዝገቡን ዘግቶ ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ እንደሚሰጥ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይም 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ባቀረቡት መቃወሚያ ላይ አመልካች የበኩላቸውን ክርክር እንዲያቀርቡ ተደርጎ መቃወሚያው ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም የሚሉበትን ዝርዝር ክርክር ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የግራቀኙን የመቃወሚያ ክርክርና መቃወሚያውን ለመወሰን የሚረዳውን ማስረጃ በመመልከት መቃወሚያው በማስረጃ ተደገፈ መሆኑን በማረጋገጥ ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡ አመልካች ጉዳዩ በዚህ መልኩ መመራቱ የሙግት አመራር ሂደቱን ያልተከተለና በሥነሥርዓት ህጉ ከተቀመጠው አካሄድ የወጣ መሆኑን በመጥቀስ ቢከራከሩም የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ብይን የሰጠው ከፍሲል የተጠቀሰው የሥነ ሥርዓት ህጉ ድንጋጌ የዘረጋውን ሥርዓት ተከትሎ በመሆኑ የቀረበው ክርክር ህጉን መሰረት ያደረገ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በሌላ በኩል ተወርሰው የነበሩ የቤተክርስቲያኗ ንብረቶች በመንግስት ውሳኔ ሲመለሱ የንብረቶቹን አስተዳደር በተመለከተ በቤተክርስቲያኒቱ ማዕከላዊ አሰራር ሥር ሆነው እንዲያዙ በቅዱስ ሲኖዶሱ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ በሥር ፍርድ ቤት የተረጋገጠ ሲሆን፤ ቤተክርስቲያኗ ከቅዱስ ሲኖዶስ እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲን ከላይ ወደታች የሚወርድ መዋቅር ያላት መሆኑና አመልካችም ሃይማኖታዊ ተዋረዱን ጠብቆና መንፈሳዊ ልጅነቱን አክብሮ መኖሩ ግራ ቀኙን ያላከራከረ በመሆኑ፤ ቅዱስ ሲኖዶስ በቤተክርስቲያኒቱ የመጨረሻው ከፍተኛው የስልጣን ባለቤት እንደመሆኑ መጠን የንብረቶቹን አስተዳደር በተመለከተ የሰጠው ውሳኔ ከቅዱስ ሲኖዶስ በታች ያሉት መዋቅሮች ሊያከብሩት የሚገባና ተፈፃሚነት ያለው መሆኑም ግንዛቤ የተወሰደበት በመሆኑ አጥቢያው ቤተክርስቲያን በሆነችው የአሁን አመልካች እና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መካከል ሊኖር የሚችለውን ከቤተክርስቲያኗ የውስጥ የንብረት አስተዳደር ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ፍርድ ቤቶች ተቀብለው በማከራከር ውሳኔ መስጠት የሚችሉ መሆን አለመሆኑን በማየት የሥር ፍርድ ቤቶች በደረሱበት መደምደሚያ የተፈፀመ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርመር ተገቢ ይሆናል፡፡

በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1) ሥር ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ ይህ መብት በህግ ሰውነት የተሰጣቸው አካላትንም የሚያካትት ነው፡፡ ስለሆነም የተፈጥሮም ይሁን በህግ የሰውነት መብት ያለው አካል በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ አቅርቦ ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡ በሌላም በኩል ከፌዴራል ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ህገ መንግስት መሰረታዊ መርሆች አንዱ የመንግስት እና ኃይማኖትን መለያየት የተመለከተ ሲሆን መንግስትና ኃይማኖት የተለያዩ መሆናቸው፣ መንግስት በሀይማኖት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ፣ ሀይማኖትም በመንግስት ጉዳይ ጣልቃ እንደማይገባ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 11(1) እና (3) ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ በአመልካች እና በ1ኛና 2ኛ ተጠሪዎች የቀረበው ክርክር በአመልካች እንደተጠቀሰው ተራ የንብረትና የይዞታ ክርክርን የሚመለከት ሳይሆን በህገ ቤተክርስቲያኗ የሚወሰኑ የቤተክርስቲያኗንና አድባራቷን ንብረቶች አስተዳደር፣ ቤተክርስቲያኗ ከቅዱስ ሲኖዶስ እስከ አጥቢያ ቤተክርስቲን ከላይ ወደታች ያላትን መዋቅር፣ በቅዱስ ሲኖዶሱ የሚተላለፉ መመሪያዎች እና ውሳኔዎች በቤተክርስቲያኗ ሥር ባሉ ገዳማት፣ አድባራት እና አጥቢያ ቤተክርስቲያናት የሚኖረውን ተፈጻሚነት ሁሉ የሚመለከት በመሆኑ የመንግስት አንዱ አካል በሆነው ፍርድ ቤት ክርክሩ ታይቶ ህገ ቤተክርስቲያኗም ተተርጉሞ የሚወሰንበት የህግ ምክንያት የለም፡፡

ስለሆነም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት ባሳለፈው ብይን እና ይግባኙ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ብይኑ ጉድለት የለበትም በማለት ባሳለፈው ትዕዛዝ የተፈፀመ የህግ ስህተት የለም ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነ ድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እ ንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 10641 ጥቅምት 18 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 119824 ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በአመልካች የቀረበው ጉዳይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓትና በህገ ቤተክርስቲያኗ መሰረት እልባት ከሚያገኝ በቀር የመንግስት አንዱ አካል በሆነው ፍርድ ቤት የሚወሰን አይደለም ብለናል፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ዐ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም